# የሁከቱ ጠንሳሾችና መሪዎች  ለፍርድ ይቅረቡ

ለሚ ዋቄ

ትግራይ ኦንላይን January 1, 2016

ክፍል አንድ

በወርሃ ህዳር በ10ኛው ቀን በባህዳር ከተማ ከአጠቃላይ የከተማው ህዝብ ጋር ሲነፃፀር እዚህ ግባ የማይባል ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች ሁከትና ግርግር ቀሰቀሰው እነደነበረ ሰምተናል። የሃገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ለጉደዳዩ ብዙም ክብደት ባይሰጡትም የሻአቢያ ተላላኪ ሚዲያዎች ግን “ሲሳይ ወረደ” በሚል  ስሜት አሸቃብጠዋል። ለሻአቢያና ለተላላኪዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀሰቀስ፣ ልማት ሊያደናቅፍ፣ የሰው ህይወት ሊያጠፋ፣ አካል ሊያጎል፣ ንብረት ሊያወድም፣ . . . የሚችል ሁከት ትልቅ ሲሳይ ነው። ታዲያ እነዚህ ሁከቱን እንደሲሳይ ቆጥረው ያሽቃነጡ ሚዲያዎች ለሁከቱና ለህገወጥ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መነሻ ነው ያሉትንም ምክነያት ነግረውናል።

በሻአቢያ ገንዘብ  ድጋፍና በሸአቢያ የፕሮፓጋንዳ አቅጣጫ ቀራጭነት የሚንቀሳቀሱት በውጭ ሃገር የሚገኙ ሚዲያዎች የህገወጡ ሁከት መነሻ ነው ያሏቸውን ሁለት ምክንያቶች ነበር የነገሩን። አንደኛው “በባህዳር ከተማ 04 ቀበሌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ የጥምቀት ታቦት ማደሪያ ስፍራ ለባለሃብት ተሰጠ” የሚል ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ “ዳመራ የሚበራበት የመስቀል አደባባይ ሊፈርስ ነው” የሚል ነው። አንዳንዱ ሰው የሁከቱን ምክንያት የመጀመሪያውን ሲያደርገው ሌሎች ደገሞ ሁለተኛው እነደሆነ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ቁርጥ ያለውን ምክንያት የሚያውቅ የለም። ለሁከት የወጡትም አያውቁትም።

ሁለቱም ምክንያቶች ግን ትክክል አልነበሩም። ሁለቱም ምክንያቶች ተቃውሞ ለመቀስቀስ ሆን ተበለው እውነታን ያለወጉ አጣሞና ኢጋኖ የተለየ ገፅታ በመስጠት፣ እንዲሁም በመፍጠር በህዝብ ውስጥ የተነዙ ናቸው። ከእነዚህ በሁከት ምክንያትነት ከቀረቡ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ አንድ እውነት ግን አለ። ይህም የባህዳር ከተማ አስተዳደርና የክልሉ መንግስት ከተማዋን በማሳደግ ለኑሮና ለስራ አመቺ ለማድረግ ሰፊ የልማት ስራ በማከናወን ላይ መሆናቸው ነው። በባህዳር ከተማ መነገዶች ይሰራሉ፣ ነባር መንገዶች ደረጃቸው ይሻሻላል፣ ህንፃዎች ይገነባሉ፣ አዳዲስ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ተቋማት ይመሰረታሉ ወዘተ። ይህ የማያቋርጥ እድገት የከተማዋ መገለጫ ለመሆን በቅቷል።

ባህርዳር ከተማ ባለፉ ሁለት አስርት አመታት በዚህ የማያቋርጥ ሂደት ውስጥ ነው ያለፈችው። ታዲያ በእነዚህ አመታት ውስጥ ከትንሽ ከተማነት ተነስታ ወደትልቅ ዓለም አቀፍ ከተማነት ለማደግ ችላለች። ባህዳር አሁን ትላልቅ ሃገር አቀፍና አለም አቀፍ ኮንፈረንሶች የሚካሄዱባት ከምስራቅ አፍሪካ ውብና ምቹ ከተሞች አንዷ ለመሆን በቅታለች።

ባህርዳር ለዚህ እድገት የበቃችው ህንፃዎቿ፣ መንገዶቿ፣ ተቋማቶቿ ድንገት ከሰማይ ዘንበው፣ ወይም ከምድር ፈልቀው አይደለም። የከተማዋ አስተዳደርና የአማራ ክልል መንግስት ከተማዋንና ክልሉን ለማሳደግ፣ የህዝቡን ኑሮ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር አስበው ሆን በለው ባከናወኑት ተግባር ነው። የልፋትና የህዝባዊ ወገንተኝነት ጥረት ውጤት ነው።

እንግዲህ የሰሞኑ ውዥንብር ይህን ልማት መነሻ ያደረገ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በተላያዩ ዘርፎች የሚካሄዱ የልማት ስራዎች አንድ ጠንካራ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ በመመስረት ሰላም ያላት ጠንካራና የበለፀገች ኢትዮጵያን የመመሰረት ሚና አላቸው። ይህ ዝንተ ዓለም በድህነት ውስጥ ለኖሩት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የሚጓጉለት ትልቅ ስኬት የመሆኑን ያህል እሳት ላይ የተጣዱ ያህል የሚያንገበግባቸው ወገኖች አሉ፤ ውጪያዊ ወገኖች። ቀዳሚው የኤርትራው ሻአቢያ ነው። የኢትዮጵያ ከተማዎች አቧራ የሚቦንባቸው መሪሳ ቤቶች የተገጠገጡባቸው ያረጁ መንደሮች ሆነው እንዲቀሩ፣ በስራ አጥ የተሞሉ፣ ጉስቁልና ቤቱን የሰራባቸው እንዲሆኑ ይመኛሉ። ድህነትና ኋላ ቀርነት ገር ለማተራመስ የሚያስችለ ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር። ስለዚህ ልማቱ በተገኘው መንገድ በሙሉ መደነቃቀፍ፣ መቋረጥ አለበት።

በኢትዮጳያ የሚካሄዱትን በተለይ በከተማዎች አካባቢ የሚካሄዱትን የልማት ስራዎች ለማደናቀፍ ሻአቢያ በተላላኪዎቹ አማካኝነት የሚጠቀምበት አንዱ ስልት ለልማት የሚሰጥ አዲስ ቦታም ሆነ በመልሶ ግንባታ ለልማት የሚውል አካባቢ ነዋሪዎች ውስጥ ውዥንብር መንዛት ነው። “መሬታቸው ተነጠቀ፣ ቤታቸው ፈረሰ፣ ተፈናቀሉ፣ . . .” የሚል ውዥንብር ህዝቡ ውስጥ መንዛት ውዥንብሩን ተቀበለው በውጭ ሃገር በሚገኙ ሚዲያዎቻቸው በማስተጋባት ሁከት ማራገብ አይነተኛና የተለመደ ስልታቸው ነው። እዚህ ላይ በተለይ ከመልሶ ማልማት ጋር በተያያዘ ምንም ችግር አጋጥሞ አያውቅም እያልኩ እንዳልሆነ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ። በመልሶ ማልማት፣ ይኖሩበት ከነበረ አካባቢ የተነሱ ሰዎች ተገቢውን የመኖሪያ ቦታ በወቅቱ ያላገኙበት፣ በቂ የካሳ ክፍያ ያላገኙበት እና መሰል ከአስተዳደር ጉድለትና ብልሹነት የተፈጠሩ ችግሮች አጋጥመዋል። ይህ ግን አጠቃላይ የልማቱን ግብ የህዝቡን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ያላገናዘበ ተደርጎ እንዲወሰድ ለማድረግ የሚያበቃ አይደለም።

ወደባህዳሩ ሁኔታ ስንመለስ፣ በባህርዳር ከተማ የልማት ስራ በስፋት የሚከናወን በመሆኑ ልማት ሊያስከትላቸው የሚችሉ ማናቸውንም ጉዳዮች - በጎም ክፉም ቢነገር የመደመጥ እድል አለው። በባህዳር ውስጥ “አዲስ መንገድ ሊሰራ ነው” ተብሎ ቢወራ ማንም “ውሸት ነው” ብሎ ሊጠራጠር የማይችለውን ያህል “መንገዱ ሲሰራ መንደሮች ይፈርሳሉ” የሚለውም የልማቱ መከናወን ተአማኒ ስለሆነ ተቀባይነት የኖረዋል።እናም የልማት ሰራ መከናወን መቻሉ ላይ እርግጠኝነት ላላቸው የባህዳር ነዋሪዎች “ልማቱ ይጎዳናል” ብለው በሚያስቡበት አኳኋን ነገሮች ያለወጉ ተጠምዝዘውና ተፈጥረው ተነገራቸው። “ለመንገድ ማስፋፊያ የመስቀል አደባባዩ ሊፈራርስ ነው እንዲሁም የታቦት ማደሪያ ለአልሚ ባለሃብት ሊሰጥ ነው” ተብሎ ሲነገራቸው ዓመኑ።

በዚህ ውዥንብር እውነትም የአምልኮ ስርአት የሚፈፅሙበት ስፍራ ተገቢ ባልሆነ አኳሆን የተነካባቸው የመሰላቸው በርካቶች የመኖራቸውን ያህል፣ ይህን ጉዳይ ሰበብ አድርገው የአክራሪነት አመለካከታቸውን ማራመድ የሚፈልጉ ጥቂቶች መኖራቸውም እውነት ነው። “ሃይማኖታችን ከሌሎች አመለካከቶችና ሃይማኖቶች፣ ከህግም በላይ መሆን አለበት” የሚል አመለካከት ያላቸው አክራሪዎች አጋጣሚውን ለአክራሪነት ስሜታቸው መግለጫ አድርገው የተጠቀሙበት ሁኔታ ተስተውሏል።

እንግዲህ በህዝቡ ውስጥ የተፈጠረው ልማትን መነሻ ያደረገ የተቃውሞ ስሜት በዚህ አኳኋን ነው የተፈጠረው። ይህ ተቃውሞ ህገመንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት የተካሄደ አልነበረም። ህገመንግስቱ አንቀጽ 30 "የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት" በሚል ርእስ ስር፤

- *ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው:: ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ::*
- *ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም::*

ተብሎ ተደንግጓል።

በባህርዳር ከተማ ከዚህ ቀደም በዚህ በህገመንግስቱ ድንጋጌ ላይ በተነገገው መብት መሰረት ሰላማዊ የተቃውሞ ሰለፎች ተካሂደዋል። በፌደራል መንግስት ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ጭምር ወደባህዳር በመሄድ የተቃውሞ ሰልፎችን አካሂደዋል። በቅርቡ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ዓለምነው መኮንን ትምክህተኝነትን በመቃወም በአንድ አጋጣሚ የገለፁትን ሃሳብ በመቃወም አንድነት፣ መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ በጋራ በመሆን ያካሄዱትን የተቃውሞ ሰልፍ ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል። በነገራችን ላይ ይህ በሆነ በጥቂት ግዜ ውስጥ አቶ ዓለምነው "ፀያፍ ነው" ብለው ያወገዙትና "ለምን ፀያፍ ተባለ" በሚል ፓርቲዎቹን ያስቆጣው የትምክህት ስሜት በባህዳር ከተማ በይፋ ተገልፆ በመላው ሃገሪቱ የማይፈለጉ ሁኔታዎች ወደማስከተል ሊሸጋገር እንደነበረ ይታወሳል።

ከዚህ ቀደም በባህዳር ከተማ የተካሄዱት ሰለፎች ሰልፉን የጠራው ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሰልፉን ለምን ዓላማ እነደሚያካሂደው፣ በሰልፉ ላይ ምን ያህል ሰው ይወጣል በሎ እንደሚጠብቅ፣ ሰልፉ የሚካሄድበትን ስፍራ፣ በሰለፉ ላይ የሚስተጋቡትን መፈክሮች ወዘተ አሳውቆ ሰልፉ በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ አስፈላጊው ጥበቃም እንዲደረግለት ለከተማው አስተዳደር በማሳወቅ ነው የተካሄዱት።

እነዚህ የተቃውሞ ሰለፎች መንግስትንና የልማት ስራዎችን የሚያወድሱ፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን እኩልነት የሚያንፀባርቁ ፣ በአጠቃላይ መንግስትንና ሀገመንግስታዊ ስርአቱን የሚያወድሱ አልነበሩም። ተቃውሞዎች ነበሩ። ይህን የማድረግ ህገመንግስታዊ መብት ስላለ የከተማው አሰተዳደር ህገመንግስቱን ለማስፈፀም ባወጣው ደንብ መሰረት የተቃውሞ ሰልፎቹ ተካሂደዋል።

የሰሞኑ የተቃውሞ ሰልፍ ግን ይህን ህጋዊ ስርአት አልተከተለም። ለተቃውሞ የወጣው ህዝብ ማን ለተቃውሞ እንደጠራው አያውቅም። ምን እንደሚቃወም አያውቅም። ተቃውሞውን ማን እንደሚመራውና በየትኛው አካባቢ እነደሚከናወን

በሰላማዊ እንቅስቃሴ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተፅእኖ . . . አይታወቅም። በመሆኑም ከመነሻውም በባህርዳር ከተማ ህዳር 10፣ 2007 ዓ/ም የተካሄደው ሰልፍ ሕገወጥ ነበር።

የተቃውሞ ሰልፉ ህግና ስርአት ተከትሎ ያልተካሄደው በውሸት ላይ የተመሰረተ፣ ዓላማውም ረብሻ በመፍጠር የሰዎች ህይወት እንዲጠፋ፣ አካል እንዲጎል፣ ንብረት እንዲወድም፣ ይህ ባልሆነ አቅጣጫ ተተርጉሞ ወደሌሎችም አካባቢዎች እንዲዛመትና በአጠቃላይ የሃገሪቱ ሰላም እንዲናጋ ልማት እንዲደናቀፍ፣ ሕገመመንግስታዊ ስርአቱ እንዲናጋ ለማድረግ ነው። በቅድሚያ በባህርዳር ከተማ ሊሰራ የታቀደው መንገድ መስቀል አደባባዩን የሚያፈርሰው አይደለም። በመጠኑ አንድ አራት ሜትር ያህል እንደሚነካው ነው መረጃዎች የሚያመለክቱት።

ይህ ስፍራውን መስቀል አደባባይ ሆኖ እንዳያገለግል የሚያደርግ አይደለም። እንዲያውም በአካባቢው ያለውን የትራፊክ እንቅስቃሴ በማሳለጥ በስፍራው ላይ በአመት አንዴ የሚከበረውን ስርአት ውብና የተቀላጠፈ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ የከተማው አስተዳደር በስፍራው የሚከናወነውን የልማት ስራ ሃይማኖታዊ ስርአቱን ከሚያስፈፅመው የቤተክህነት አመረሮች አሳውቆ የሁንታን አግኝቷል። እናም "በመንገድ ግንባታ ምክንያት መስቀል አደባባዩ ሊፈርስ ነው" የሚለው ወሬ መሰረተ ቢስና ውሸት ነበር።

የተወሰኑት በህገወጥ ተቃውሞው ላይ የተሳተፉ ገለሰቦች ለተቃውሞ የወጡበት "የታቦት ማደሪያ የሆነው ስፍራ ለአልሚ ባለሃብት ሊሰጥ ነው" የሚለውም ሃሰት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም የሚታወቅ ነገር የለም። ጉዳዩ ህዝብን አስኮርፎ ለተቃውሞ ሊያስነሳ የሚችል በመሆኑ ተፈጥሮ የተነዛ ነው።

በሃሰተኛ ጉዳይ ላይ የተመሰረተው የተቃውሞ ሰልፍ የተካሄደበትም መንገድ ሕገወጥ ነበር። ለተቃውሞ አደባባይ የወጡት ሰዎች የከተማውን መንገድ በመዝጋት የትራፊክ እንቅስቃሴ ከማቋረጣቸው በተጨማሪ ወደክልሉ አስተዳደርና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዳራሽ በመሄድ በጥበቃ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ላይ እንዲሁም ፀትታን ለማስከበር የቆሙ የፖሊስ ሰራዊት አባላት ላይ የድንጋይ ኡሩምታ በማውረድ በአካልና በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ ሞክረዋል። ይህ በህገወጥ መንገድ የተጠራው ተቃዋሚ የወሰደው እርምጃ ህገወጥ - ወንጀል ነው። በሕግ ያስጠይቃል።

አዋኪዎቹ በወሰዱት የሃይል እርምጃ ንብረት ወደሟል፤ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደረሷል። ይህ ህገወጥ መነሻ ያለውና ህገወጥ በሆነ መንገድ የተካሄደው ሁከተና ግርግር በሰው ህይወትና አካል፣ በህዝብና በግለሰቦች ሃብትና ንብረት ላይ የከፋ ጉዳት ከማድረሱና ሰላማዊ እንቅስቃሴን በመገደብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ከመፍጠሩ በፊት መቀልበስ ነበረበት። መንግስት ይህን የማድረግ ሃላፊነት አለበት፣ ህጋዊ ስልጣንም አለው። ይህን ሳያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ ሰላምና ፀትታ የማስከበር ሃላፊነቱን ባለመወጣት ይጠየቃል።

በዚህ ህገወጥ ሁከትና ግርግር ምክንያት የአንድ ሰው ህይወት ጠፍቷል። አምስት ስድስት የሚሆኑ ላይ ደግሞ ቀላል የመቁሰለ አደጋ ደርሷል። ይህ የህይወት መጥፋትና የመቁሰል አደጋ በአዋኪዎቹ የሃይል እርምጃ የተፈፀመ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። የፀጥታ አስከባሪዎችን መሳሪያ እስከመቀማት ወይም በመሳሪያ የታገዘ ጥቃት በሌሎች ላይ

ለመፈፀም የሚደረግ ሙከራን በተመጣጣኝ ሃይል ለመከላከል በተወሰደ እርምጃ ያጋጠመም ሊሆን ይችላል። ይህ እስካሁን ተጣርቶ የፋ አልተደረገም።

ቀደም ሲል በፅሁፉ መግቢያ ላይ እንደጠቀሰኩት በውጭ የሚገኙ በሻአቢያ የገንዘብ ድጋፍና የአፍራሽ ፕሮፓጋንዳ አቀጣጫ ነዳፊነት አይናቸውን ጨፍነው የሚለፈልፉ በውጭ ሃገራት ያሉ ሚዲያዎች "ያሰብነው ተሳካ" በሚል ስሜት አሽካኩ፣ አሽቃነጡ። ሁከቱ እንዳይበርድ፣ እልቂቱ እንዲባባስ ማራገቡን ተያያዙት። በዕለቱ ባሰራጩት ዘገባ "በሁከቱ የአምስት አንዳንቹም የሰባት ሰዎች ህይወት ጠፋ" የሚል ዘገባ አሰራጩ። ተቃውሞውን የህዝብ ተቃውሞ አድርገው ለማቅረብም ሞከሩ።

ይሁን እንጂ ህገወጡ ተቃውሞ ጥቂቶች የተሳተፉበት በመሆኑ መንገድ በመዝጋትና ድንጋይ በመወርወር ወዘተ የሃይል ጥቃትም ለመፈፀም ቢሚከረበትም የከፋ ጉዳት ሳያስከትል በቁጥጥር ስር መዋል በመቻሉ ወዲያው ከሰመ። ህገወጥ ተቃውሞውና ተቃውሞው የቀሰቀሰውእንዲሁም የከተማው  ሁከት መክሰሙን ተከተሎ የኦረቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት አባቶችና የከተማው አስተዳደር ፖሊሰ መግለጫ ሰጡ።

የሃይማኖት አባቶች "ሊፈርስ ነው" የተባለውን መስቀል አደባባይ በተመለከተ በሰጡት መግለጫ፣ የከተማ አስተዳደሩ በመስቀል አደባባዩ አቅራቢያ ሊሰራ ባሰበው የመንገድ ማስፋፊያ የልማት ስራ ዙሪያ ጉዳዩን አቅርቦላቸው መወያየታቸውን፣ በዚህ ውይይትም የማስፋፋቱ ስራ በመስቀል አደባባዩ ላይ ምንም ተጨባጭ ጉዳት እንደማያስከትል በመተማመን መግባባት ላይ መድረሳቸውን ገልፀው አስተዳደሩ አክብሮ አስቀድሞ ጉዳዩን አሳውቆ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ለማድረጉ አመስግነዋል፤ መርቀዋልም።

የሃይማኖት አባቶቹ መግለጫ በከተማዋ የተቀሰቀሰው ህገወጥ ተቃውሞ ልማትን ለማደናቀፍና የራስን ዓላማ ለማሳካት ያለመ በመሆኑ የሃይማኖቱን ተከታዮች እንደማይወክል፣ ሊወገዝ እንደሚገባውም አስታውቀዋል። ቤተክርስቲያኒቷም ሆነች ህዝበ ክርስቲያኑ ተቃውሞውን እንደማይደግፉ መግለጫው በይፋ አስታውቋል። ቤተክርስቲያኗ እንደገለፀችው የተቃውሞ ጥያቄው የህዝበ ክርስቲያኑ ጥያቄ አይደለም። የሌሎች ሃይማኖት ተወካይ የሆኑ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችንም አይመለከትም። እናም የህዝብ ጥያቄ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ህገወጥ ተቃውሞውን መነሻ በማድረግ ባወጣው መገለጫ እውነት ጥያቄው የህዝብ ከሆነ መንገድ ያማስፋፋቱ የልማት ስራ ሊቋረጥ እንደሚችል አስታወቀ። መንገዱ ይሰራ ወይም ባለበት ይኑር የሚለው ጉዳይ በዋናነት የሚመለከተው የባህዳር ከተማ ህዝብ ነው። መንግስት የህዝቡን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፍላጎቶች የማስፈፀም ሃላፊነት ነው ያለበት። የባህዳር ህዝብ "ልማቱን አልፈልግም" በሎ ከወሰነ የህዝብ ውሳኔ በመሆኑ አሰተዳደሩ ከመቀበል ውጭ አማራጭ የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጥያቄው ከቀረበ ልማትን በመቃወም የቀረበ የመጀመሪያው የዓለማችን ጥያቄ ሆኖ ይመዘገባል።